THE JOINT COUNCIL *for* THE WELFARE OF IMMIGRANTS

# ስለ ኢሚግረሽን ጉዳይ የሕግ ድጋፍ ለማግኘት

በሕጋዊ መንገድ ፍትሕ ለማግኘት የሚረዳ ተግባራዊ መመርያ

2023



# መግቢያ

ይህ መመሪያ በዩናይትድ ኪንግደም የስደት ሁኔታቸው በሚመለከት ችግር ላጋጠማቸው ሰዎች ይመለከታል።

ይህ ደረጃ በደረጃ መመሪያ ከስደት ጠበቆች ጋር ለመስራት እና ፍትህ እንድታገኙ ይረዳችሁ ዘንድ ነው። የሚሸፍነው፡-

- ከጠበቃ ምን እንደሚጠበቅ
- ጠበቃ ከእርስዎ ምን እንደሚጠብቅ
- ከጠበቃዎች ጋር ግንኙነቶችን ማዳበር ወይም ማሻሻል
- በጠበቃ ካልተደሰቱ ምን ማድረግ እንዳለበት

“ሰዎች፡ እውቀት ያለው ሰው ህጋዊ ሂደቱን መርምሮ ውጤታማ የህግ ውክልና ሊያደርግ እንደሚችል ኣውቀው ድህንነት ሊሰማቸው ይገባል”

- JCWI ደንበኛ

# ይዘቶች


መግቢያ ..... 1
የሕግ ጉዳይ ምንድነው? ..... 3
የሕግ ጠበቆች ኣና የስደተኞች ኣማካሪዎች ምን ያደርጋ? ..... 3
የኣማካሪዎች ዓይነቶች ..... 3
ጠአቆች ..... 3
የኢምግረሽን ኣማካሪዎች ..... 3
የግል ጠበቆች ..... 4
በነጻ ወይም በቅናሽ (ፕሮ ቦኖ) የሚያገለግሉ ጠበቆች ..... 4
ጠበቆች (በፍርድ ቤት ሂደት) ..... 4
የሕግ ምክር እና የሕግ እገዛ ..... 4
የሕግ እርዳታ ..... 5
የሕግ እርዳታ ምንድነው (ሌጋል አይድ)? ..... 5
የሕግ እርዳታ ምን ዓይነት ጉዳዮችን ይሸፍናል? ..... 6
ሌሎች መስፈርቶች ምንድን ናቸው? ..... 6
የሕግ እርዳታ መጠየቅ ..... 7
ለየት ላለ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ ..... 7
ለየት ላለ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ..... 7
ለ ECF ማመልከቻ ማቅረብ ..... 7
የሕግ ተወካይ ብቁ መሆኑን ማረጋገጥ ..... 8
የሕግ ተወካይ ማግኘት ..... 8
የመጀመርያ ግንኙነት ከጠበቃዎ ጋር ..... 9
ዝምድናዎ ከጠበቃዎ ጋርc ..... 10
የደንበኛ ስልጣን ደብዳቤ ..... 10
የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ..... 10
ከጠበቃ ጋር መስራት ..... 11
ከጠበቃ ምን መጠበቅ ይችላሉ ? ..... 11
ጠበቃዎ ከእርስዎ ምን ይጠብቃል? ..... 11
ጠበቃና ደንበኛ ግንኙነት – ኣጠቃላይ መመርያ ..... 12
በሕግ ኣማካሪይዎ ካልተደሰቱ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ..... 12
ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችና ማእከሎች ..... 13

# የሕግ ጉዳይ ምንድን ነው?

የሕግ ጉዳይ ሕግን ተጠቅሞ ሊፈታ የሚችል ችግር ነው : ጉዳዩን ለመፍታት የሕግ አማካሪ ያስፈልግዎት ይሆናል። አንዳንድ ቁልፍ የሕግ ጉዳዮች እነዚህን የጠቃልላሉ፥

- **ኢሚግረሽን** – በእንግሊዝ አገር የመኖርያ ፈቃድ ማግኘት ወይም መጠበቅ ወይም ማረጋገጥ።
- **ወንጀል** – በወንጀል ድርጊት ከተከሰሱ
- **መኖርያ ቤት**– የመኖርያ ቤት ችግር ካልዎት ችግሩ ለመፍታትየሕግ አማካሪ ያስፈልግዎት ይሆናል
- **ስራ** –በስራዎ ላይ ችግር ካጋጠምዎት፡ ለምሳሌ በስራ ቦታዎ አድልዎ የሚፈጸምብዎ ከሆነ ፍትህ እንዲያገኙ ጠበቃ ሊረዳዎ ይችላል

# ጠበቆች እና የሕግ አማካሪዎች ምንድነው ስራቸው?

ጠበቃ ወይም የኢሚግሬሽን አማካሪ ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ያደርጋል። የተገደበ ዝርዝር የለም፡ ነገር ግን በዋናነት የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥-

- **ከደንበኞች መመሪያዎችን መውሰድ፥** - ይህ ማለት ችግርዎን ማዳመጥ እና ያዳመጡትን ማስታወሻ መውሰድ ማለት ነው።
- **ያማክርዎታል**~ ሊሆኑ ስለሚችሉ ድርጊቶች
- **ሁሉንም ግንኙነትና ሰነዶች መቋቋም።** ጉዳይዎን በሚመለከት
- **አስፈላጊ ማስረጃዎችን ሰብስቦ ጉዳይዎን ለፍርድ ቤት ያዘጋጃል።** አስፈላጊ ከሆነ እና ጉዳይዎ ወደ ፍርድ ቤት የሚሄድ ከሆነ ባሪስተር የሚባል ጠበቃ ያስፈልግዎት ይሆናል (ገጽ 4 ይመልከቱ).

# የአማካሪ አይነቶች

## ጠበቆች

**ጠበቃ** የሕግ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ነው። ጠበቃ በተለያየ የሕግ ዘርፍ ስፐሽያላይዝ ማድረግ ይችላል። ከዚህ በላይ በተገለጸው ችግር ካለብዎት ጠበቃ ሊረዳዎት ይችላል። በሕግ አማካሪዎች ደንብ ማለስልጣን (SRA) የተረጋገጠላቸው ብቻ ጠበቃ ተብለው ይጠራሉ። ብቁ መሆን፡ ስነ ምግባር ያላቸው እና የ (SRA) ሕግ የሚከተሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

ጠበቆች በሕጋዊ ድርጅቶች በግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ወይም ብ አካባቢ ባለስልጣን ሊሰሩ ይችላሉ።

ሁሉም ጠበቆች በSRA መመዝገብ አለባቸው። የህግ ጠበቃ ነኝ ከሚል ሰው ጋር እየሰሩ ከሆነ በSRA መዝገብ ስማቸውን https://www.sra.org.uk/consumers/register ውስጥ በማስገባት ማረጋገጥ ይችላሉ። ሁሉም የተመዘገቡ የህግ አማካሪዎች ልዩ የምዝገባ ቁጥር አላቸው - ይህንን እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ፣ በዚህም ብቃታቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

# የኢሚግረሽን አማካሪዎች

ሁሉም የህግ ችግሮች ጠበቃ አያስፈልጋቸውም - **ከኢሚግሬሽን አማካሪ** ድጋፍ ማግኘት ይችሉ ይሆናል። ይህ የኢሚግሬሽን ምክር ለመስጠት ብቁ የሆነ ሰው ነው፣ ነገር ግን ጠበቃ አይደለም። ሆኖም፣ የኢሚግሬሽን ምክር የሚሰጣችሁ ሰው ትክክለኛ መመዘኛዎች እንዳለው ማረጋገጥ ይኖርብዎታል።

**በይፋ ያልተመዘገበ ሰው በኢምግረሽን ጉዳይ የሚሰጠው ምክር በነጻ ቢዮንም ህጋዊ አይደለም።** በዩናይትድ ኪንግደም የጥገኝነት፣ የኢሚግሬሽን ወይም የዜግነት ምክር የሚሰጥ ማንኛውም ሰው እንደ ጠበቃ ወይም ባሪስተር፣ **ወይም በስደተኛ አገልግሎት ኮሚሽነር (OISC) ቢሮ ወይም በሕግ አስፈፃሚዎች ተቋም መመዝገብ ይኖረበታል።**

አንድ ሰው የኢሚግሬሽን ምክር እሰጥዎታለሁ ካለ፣ የድርጅታቸውን ስም በ OISC ድረ-ገጽ https://home.oisc.gov.uk/register_of_regulated_immigration_advisers/register.aspx ላይ በማስገባት ብቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

## የግል ጠበቆች

ብዙ ሰዎች **የሕግ እርዳታ** ማግኘት ካልቻሉ የህግ ምክር ለማግኘት መክፈል አለባቸው (ገጽ 5 ይመልከቱ)። የሕግ ምክር ለማግኘት፣ የግል ጠበቃ ማግኘት አለባቸው።

የግል ጠበቃ ማድረግ ትልቅ ውሳኔ ነው ምክንያቱም ውድ ሊሆን ስለሚችል ብቻ ሳይሆን ሕጋዊ መዘዝ ሊያስከትል ስለሚችል ነው.

አንዳንድ የሕግ ድርጅቶች የተወሰነ ክፍያ ስምምነት የሚባል ነገር አላቸው፣ ይህ ማለት እርስዎ በተስማሙበት ማመልከቻ ወይም የጉዳይዎ አንድ ክፍል ላይ ብቻ እንዲሰሩ የተወሰነ መጠን ይከፍሏቸዋል። ከአንዳንድ ድርጅቶች ጋር፣ በአከፋፈል ደረጃ መክፈል ይችላሉ፣ ሌሎች ደግሞ 'ካላሸነፍክ አትከፍልም' በሚል ስምምነት ላይ ይሰራሉ።

በድጋሚ፣ ከእውነተኛ እና ታዋቂ የሕግ ድርጅት ጋር እየሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። በመስመር ላይ የአማካሪውን ልምድ እና መመዘኛዎች መመርመር ይቻላል።ዋጋቸውእና የሚያቀርቧቸውን አገልግሎቶች ለመወያየት በቀጥታ እነሱን ማግኘት አለብዎት እና ዋጋቸውን በመስመር ላይ ከሚያስተዋውቁ ሌሎች ድርጅቶች ጋር ማወዳደር ይችላሉ። በዋጋው ውስጥ ምን እንደሚያካትት እና ሌላ ተጨማሪ ክፍያ እንዳይኖረው ግልጽ መረጃ መስጠት አለባቸው።

የግል ጠበቃ መክፈል ካልቻሉ እና ፕሮ ቦኖ ጠበቃ ማግኘት ካልቻሉ (የሚቀጥለውን ክፍል ይመልከቱ)፣ አሁንም አንዳንድ አማራጮች ማፈላለግ ይችላሉ። የአካባቢ በጎ አድራጎት ድርጅትን ማነጋገር ይችላሉ፣ እና ለሕጋዊ ክፍያዎች ገንዘብ ለማሰባሰብ ሊረዱዎት ይችላሉ። እንዲሁም ከቤተሰብ ወይም ከጓደኞች እርዳታ መጠየቅ ወይም ወደ ከአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ወይም የአምልኮ ቦታ መጠየቅ ትችላላችሁ።

## ፕሮቦኖ ጠበቃዎች

'**ፕሮ ቦኖ**' የሚባል ነገር የሕግ እርዳታ ለማግኘት ሌላ አማራጭ ነው። ፕሮ ቦኖ ጠበቃ ለጠቅላላው ጉዳይዎ በነጻ ሊሰራልዎት ወይም ሊወክልዎ ይችላል። ይሁን እንጂ ፕሮ ቦኖ ጠበቃ ማግኘት በአቅም ማነስ ምክንያት በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። በአካባቢዎ ያሉ ትልልቅ የሕግ ድርጅቶችን ፈልገው በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ፕሮ ቦኖ ላይ የሚሰሩ ከሆነ ለማየት ድህረ ገጻቸውን መመልከት ይችላሉ።

## ባሪስተሮች

**ባሪስተር** ልዩ የሕግ ምክር ይሰጣል ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን በፍርድ ቤት ይወክላል። ሰዎች ጠበቆችን 'ካውንስል' ሲክዋቸው ሊሰሙ ይችላሉ - ይህ የባሪስተር ሌላ ቃል ነው። ፍርድ ቤት ደንበኞቻቸውን ይወክላሉ፡ ምስክሮችን ይመረምራሉ እና ዳኛውን ያናግራሉ። ለማጠቃለል፣ በጉዳይዎ ላይ የጀርባ ስራ የሚሰራው ጠበቃ ነው፣ እና እርስዎን በፍርድ ቤት የሚወክለው ባሪስተር ወይም ካውንስል ነው።

# የሕግ ምክር እና የሕግ ድጋፍ

**በሕግ ምክር** እና **በሕግ ድጋፍ** መካከል ልዩነት አለ። የህግ ምክር ማለት አግባብነት ያላቸውን ህጎች, ደንቦች እና መርሆዎች መተግበር እና የእርምጃ መንገድን ሀሳብ ማቅረብ ማለት ነው። [1].

የኢሚግሬሽን ምክር ለመስጠት ጠበቃ መሆን አያስፈልገዎትም፣ ነገር ግን OISC የሚፈቅደው መመዘኛዎች ሊኖርዎት ይገባል፣ ወይም በSRA መመዝገብ አለብዎት። ብቃት ከሌለው ሰው መደበኛ

[1] *Legal Advice Right to Remain: https://righttoremain.org.uk/toolkit/yourlegalcase*

ያልሆነ ምክር መቀበል ምክር ካለመቀበል የከፋ ሊሆን እንደሚችል ያስታውሱ።

የሕግ ምክር ማግኘት ካልቻሉ፣ በምትኩ የሕግ ድጋፍ የሚባል ነገር ማግኘት ይችሉ ይሆናል። የሕግ ድጋፍ ጥብቅ ቁጥጥር የሚደረግበት አይደለም፣ እና የበለጠ አጠቃላይ ነው። የህግ ድጋፍ መስጠት ለምሳሌ:-

- ሰዎች የበለጠ እና የተለየ ምክር እንዲያገኙ ወደ ድርጅቶች ወይም በጎ አድራጎት ድርጅቶች መጠቆም።
- መመሪያዎችን፣ እንደ ከታማኝ ድርጅቶች የመጡ መሳሪያዎች በመጋራት ስለ እርስዎ ጉዳይ መሰረታዊ መረጃ ሊያስተምሯችሁ ይችላሉ።
- የምክር ማእከላትን በተመለከተ ለሰዎች መረጃ መስጠት። በ የሕግ ማእከሎች ኔትወርክ መጀመር ጥሩ ነው። https://www.lawcentres.org.uk
- አንድ ሰው በነጻ፣ በሚስጥራዊ እና በገለልተኛ ምክር ከ ሲቲዚንስ አድቫይዝ ምክር እንዲያገኝ መርዳት
- ስለ ተሟጋች መረጃ መስጠት፡ https://weareadvocate.org.uk በነጻ የህግ ምክር እና በፍርድ ቤት ጉዳዮች ከበጎ ፈቃደኛ ጠበቃዎች መታገዝ ይረዳል።
- የአካባቢ ባለስልጣናትን ማነጋገር ወይም ከሐኪምዎ፣ ማህበራዊ ሰራተኛዎ ወይም ከትምህርት ቤቶችዎ ደብዳቤ ማግኘት።
- ለከአንድ ሰው ለጥገኝነት ቃለ መጠይቅ መሸኘት ወይም ከሆም ኦፊስ ጋር ቀጠሮ መያዝ፡ እንዲህ የመሰለ የስሜታዊ ድጋፍ እንደ ህጋዊ ድጋፍ ይቆጠራል
- ለጉዳይዎ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል አጠቃላይ መረጃ ማቅረብ።

ከላይ እንደተገለጸው፣ ድጋፍ የሚያገኙባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ የአካባቢ ባለስልጣን ወይም የህግ ተቋም ሊያመለክትዎት ይችላል፣ ይህ ማለት ድጋፍ ወደሚያገኙበት ቦታ ሊጠቁምዎት ይችላል።

ሪፈራል (መጠቆም) ማድረግ ትንሽ የተለየ ሂደት ነው። እንደ አማካሪዎች፣ ማህበራዊ ሰራተኞች፣ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ወይም ሌሎች የሚደግፉ ሰዎች እርስዎን ሊጠቁሙዎት ይችላሉ። ይህ ማለት መረጃዎን ለሌላ ድርጅት ያስተላልፋሉ ማለት ነው። እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሌላ የሕግ ድርጅት፣ የአካባቢ ባለስልጣን፣ ዶክተር፣ የአእምሮ ጤና ቡድን ወይም ሌላ ማንኛውም ድርጅት ወይም ወደ የመንግስት ኤጀንሲ ሊመራዎት ይችላል። እርስዎን እየጠቀሰ ያለው ሰው እርስዎ እየተመሩ ወይም ወደ ሌላ ኣካል እየተላለፉ እንደሆነ ሊነግሩዎት ይገባል፣ እና ይህ እንዲሆን ፈቃድ እንደሰጡ ማረጋገጥ አለባቸው።

# የሕግ እርዳታ

## የሕግ እርዳታ ምንድን ነው?

Legal Aid ነፃ የሕግ ውክልና የማግኘት ሥርዓት ነው፣ በገለልተኛ ጠበቆች የሚደረግ ነገር ግን በመንግሥት የሚከፈል ነው። Legal Aid ማለት መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ሰዎች የሕግ ምክር በነጻ ማግኘት ይችላሉ። የሕግ እርዳታ የሚሰጠው **በሕጋዊ እርዳታ ኤጀንሲ** (LA) ነው።

የሕግ እርዳታ ለማግኘት ኣብዛኛውን ጊዜ የሚከተሉትን ማረጋገጥ ያስፈልግዎታል:-

- **ጉዳይዎ ብቁ መሆን።**
- **ችግሩ ከባድ ስሆን**
- **ለሕጋዊ ወጪ ራስዎን መክፈል ካልቻሉ**

ሁሉም የሕግ ድርጅቶች የሕግ እርዳታ ኣገልግሎት ኣይሰጡም። የሕግ እርዳታ ኣገልግሎት አቅራቢዎች ሕጋዊ እርዳታ ለመስጠት፡ ከሕግ እርዳታ ኤጀንሲ ጋር ውል ሊኖራቸው ይገባል። የሕግ ድጋፍ ሰጪዎች ከመንግስት እና ከሌሎች ሀይለኛ ባለጉዳዮች ሙሉ በሙሉ ነፃ ናቸው። ይህ ማለት ምንም እንኳን ከመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ቢያገኙም፡ ስራቸው ሙሉ በሙሉ ከነሱ ነጻ ነው - እርስዎን ለመወከል ይሰራሉ።

በዩኬ ውስጥ የኢሚግሬሽን መኖርያ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ጉዳያቸው መስፈርቶቹ እስካሟሉ ድረስ የህግ እርዳታ (Legal Aid) ሊያገኙ ይችላሉ። የሕግ እርዳታ እንደ የህዝብ ፈንድ አይቆጠርም

ስለዚህ ምንም የመንግስት እርዳታ ባያገኙም የሕግ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

ከሕግ እርዳታ አማካሪ ጋር ከመመዝገብዎ በፊት ትክክለኛ መመዘኛዎች እንዳላቸው ለማረጋገጥ ኣስፈላጊ ምርምር ማካሄድ አስፈላጊ ነው።

ጠበቃ ለሕጋዊ እርዳታ ማመልከቻ፣ ለየት ያለ የጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ወይም ክፍያ የመሰረዝ ማመልከቻ እንዲከፍሉ በፍጹም ሊጠይቅዎት አይገባም።

## ሕጋዊ ድጋፍ (Legal Aid) ምን ዓይነት ጉዳዮችን ይሸፍናል?

Legal Aid የሚከተሉትን የማመልከቻ ዓይነቶች ለሚያደርጉ ሰዎች ብቻ ነው የሚገኘው፡-

- **የጥገኝነት ጥያቄ**
- **የሰብአዊ ጥበቃ**
- **`ሊቭ ቱ ሪመይን`** (ቪዛ) ምክንያቱም ወደ ትውልድ ሀገርዎ መመለስ በህይወት የመኖር መብትዎን የሚጥስ ከሆነ(አንቀጽ 2) ወይም ስቃይ ወይም ኢሰብአዊ ወይም አዋራጅ አያያዝ ወይም ቅጣት እንዳይደርስብዎት መብት ስላለዎት(አንቀጽ 3)
- **በኢሚግሬሽን ዋስትና፥** በኢሚግረሽን የማስወገድ ማዕከል ውስጥ ሲታሰሩ እና መፈታት ሲፈልጉ
- **`ኢንደፊኒት ሊቭ ቱ ረመይን`** እንደ የዘቤታዊ ጥቃት ሰለባ
- **ቪዛ እንደ ብቸኛ ልጅ** - በዩከ መኖር ከፈለጉ
- **ቪዛ፥** ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የዘመናዊ ባርነት ሰለባ ሲሆኑ

## ሌሎት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

ጉዳይዎ ለህጋዊ እርዳታ ብቁ ከሆነ፡ ነጻ ውክልና ለማግኘት አሁንም ሌሎች ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት አለበት። እነዚህን ፈተናዎች እንዳሟሉ የሚወስነው የህግ ተወካይ ነው።

የመጀመርያው `ሚንስ ተስት` ተብሎ ይጠራል - ይህ የሕግ እርዳታ ኤጀንሲ ነፃ የሕግ ምክር ያስፈልግዎት እንደሆነ የሚወስንበት ነው። ስለ እርስዎ የፋይናንስ ሁኔታ (ገቢ, ደመወዝ, ጥቅማጥቅሞች, ቁጠባዎች, ንብረቶች) ማስረጃዎችን መመልከት ይኖራቸዋል።

የ`ሚንስ ተስት` ፈተና ለማለፍ ገቢዎ (ወይም በቁጥጥርዎ ያለ የካፒታል መጠን) በሕግ እርዳታ ኤጀንሲ ከተቀመጠው ገደብ ያልበለጠ መሆኑን ማሳየት አለበት።

ይህንን መመሪያ በሚጻፍበት ጊዜ በወር ከ £2657 በታች የሚያገኙ ከሆነ እና ታክስ፡ ብሔራዊ ኢንሹራንስ፣ የቤት ኪራይ፣ የስራ ወጪ እና ለቤተሰብ የሚውለው ገንዘብ በእርስዎ ላይ ጥገኛ የሆኑ ሰዎች ከከፈሉ በኋላ የቀረዎት ከ £733 የማይበልጥ ከሆነ የሚንስ ፈተናን ማለፍ ይችላሉ። የሕግ አማካሪዎ የፈተናውን ዘዴ በዝርዝር ማብራራት መቻል አለበት።

ሁለተኛው ፈተና `የመሪት ፈተና` ይባላል - ይህ የሕጋዊ ድጋፍ ኤጀንሲ ጉዳይዎ ጠንካራ እንደሆነ እና ጥሩ የመሳካት እድል ያለው እንደሆነ የሚወስንበት ነው። የ`ሚንስ ተስት` ካለፍክ፣ የ`መሪት ተስት` ጠበቃዎትም የ`መሪት ተስት` ያለፉ ከሆነ መወሰን ኣለበት። ይህ ማለት ጠበቃዎ ያናግርዎታል እና ጉዳይዎ የማሸነፍ እድሉ ምን ያህል እንደሆነ ይወስናል እና በጉዳይዎ ማሸነፍ ምን ያህል እንደሚጠቅሙ ይገልጽልዎታል ።

## ሕጋዊ ድጋፍ መጠየቅ

የሕግ ድጋፍ አማካሪ ካገኙ በኋላ ማመልከቻ ያቀርብልዎታል። ስለ ገቢዎ፣ ስለ ቁጠባዎ፣ ምንም አይነት ጥቅማጥቅሞች እየተቀበሉ እንደሆነ እና ስለ ወጪዎ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን ለእርሱ መስጠት ያስፈልግዎታል። የክፍያ ደረሰኞች እና የባንክ መግለጫዎች ካልዎትም ማቅረብ አለብዎት። እንዲሁም ናሽናል ኢንሹራንስ ቁጥር ይጠይቁ ይሆናል፣ እንዲሁም የልደት የምስክር ወረቀትዎ እና የጋብቻ የምስክር ወረቀት ሊፈልጉ ይችላሉ። የገንዘብ ሁኔታዎ ከተቀየረ በተቻለ ፍጥነት የሕግ አማካሪዎን ማስታወቅ አለብዎት።

እንደ እርስዎ ጉዳይ እና ሁኔታ፣ ለሕጋዊ ድጋፍ ሲያመለክቱ አማካሪዎ መሙላት ያለባቸው ቅጾች እነዚህ ናቸው:-

**CW1:** ይህ ቅጽ የሕግ ድጋፍ ደንበኞችን የፋይናንስ ብቁነት ይወስናል

**CW2 (IMM):** ቁጥጥር የሚደረግበት የህግ ውክልና

**Civ ECF 1:** ለየት ያለ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ (ከዚህ በታች ይመልከቱ) - ይህ ቅጽ ለየት ያለ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ የሚያመለክቱበትን ምክንያት ማካተት አለበት።

## ለየት ያለ የጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ

ከላይ ከተዘረዘሩት ማመልከቻዎች ውስጥ አንዱን ባያቀርቡም እንኳ፣ ነጻ የሕግ ውክልና ማግኘት ይቻል ይሆናል። ይህ የልዩ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ (ECF) ይባላል። ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ ወይም ለግል ህይወት ባልዎት መብት (አንዳንድ ጊዜ የአንቀጽ 8 ማመልከቻ ተብሎ የሚጠራው) የሚያመለክቱ ከሆነ፣ ህጋዊ እርዳታ ወድያውኑ የማግኘት መብት አይኖርዎትም፣ ነገር ግን ለECF ማመልከት ይችላሉ።

የሚከተሉትን ጉዳዮች ECF ማግኘት ይችላሉ:

- እንደ ኣጋር የ ሊቭ ቱ ሪመይን` ማመልከቻ ማቅረብ
- እንደ ወላጅ የሊቭ ቱ ረማይን` ማመልከቻ
- በዩኬ ውስጥ ለ20 ዓመታት ስለኖሩ የሊቭ ቱ ረመይን`ማመልከቻ
- ለልዩ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ የሚሆኑ ሌሎች የጉዳይ ዓይነቶች አሉ፣ ነገር ግን ይህ እንደየግል ሁኔታዎ ሊወሰን ይችላል።

## ለገንዘብ ድጋፍ የልዩ ጉዳዮች ብቁነት

ለECF ብቁ ለመሆን፡ ነፃ የሕግ ድጋፍ ካላገኙ ሰብአዊ መብቶችዎ እንደሚጣሱ ማሳየት አለበት።

ECF ከተሰጠዎ ነጻ የሕግ አገልግሎት እና ምናልባትም ውክልና ማግኘት መቻል አለብዎ።

## ለ ECF ማመልከቻ ማቅረብ

እርስዎ ወይም የሕግ አማካሪዎ **Civ ECF 1** ቅጽን በመሙላት ለ**ECF** ማመልከት ይችላሉ።

ማመልከቻ ለማቅረብ የሚከተሉትን ማሳየት አለበት:-

- ለሕጋዊ ችግርዎ የሕግ ድጋፍ ብዙ ጊዜ አይገኝም
- ለሕጋዊ እርዳታ በገንዘብ ብቁ ነዎት - ዝቅተኛ ገቢ ካሎት፣ ትንሽ ወይም ምንም የቆጠቡት ገንዘብ ከሌለ ወይም ውድ ንብረቶች ከሌልዎት ወይም የተወሰኑ ጥቅማጥቅሞችን የሚያገኙ ከሆነ ብቁ ይሆናሉ።
- ጉዳይዎ ስኬታማ ለመሆን የሚችል ነው።
- ያለ ጠበቃ ማመልከቻውን ማቅረብ አይችሉም፣ እና ያለ ህሕዊ እርዳታ ጉዳይዎን ማቅረብ በጣም ከባድ ነው (ወይ ጉዳይዎን በብቃት ማቅረብ አይችሉም)። ለምሳሌ ማንበብና መጻፍ እንደማይችሉ ወይም የመጻፍ ወይም የማንበብ ችግር እንዳለብዎ መከራከር ይችላሉ። እንዲሁም ደካማ የአይቲ (IT) ችሎታ እንዳለዎት፣ እንግሊዘኛ የመጀመሪያ ቋንቋዎ እንዳይደለ እና እንዳይረዱት፣ ወይም ውስብስብ ጉዳዮችን

ወይም ውስብስብ የሕግ ሂደቶችን እንደማይረዱት ብለው መከራከር ይችላሉ።

• ሕጋዊ እርዳታ ካላገኙ ሰብአዊ መብቶችዎ ሊጣሱ እንደሚችሉ።

# የሕግ ተወካይ ብቁ መሆኑን ማረጋገጥ

የሕግ ተወካይ ለማግኘት ብዙ መንገዶች አሉ። አንዳንድ ሰዎች በአካባቢያቸው ያሉ አማካሪዎችን በኢንተርኔት በመፈለግ ይጀምራሉ። ሌሎች ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ምክር ሊያገኙ ይችላሉ።

ፍለጋዎን በተለያየ መንገድ ቢጀምሩም፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፣ እና ከማድረግዎ በፊት ምርምር ያድርጉ።

1. የእነሱ ድረ-ገጽ የሚሰጡትን አገልግሎቶች ዝርዝር ይሰጣል?

2. በአማካሪዎች ቁጥጥር ባለስልጣን (SRA) ወይም በስደተኛ አገልግሎት ኮሚሽነር (OISC) ቢሮ የተመዘገቡ ናቸው?

3. የዋጋ ዝርዝራቸውን እና ስለ ሕጋዊ እርዳታ (ከሰጡ) መረጃን በዝርዝር ያሳያሉ?

4. ከታች ካሉት አርማዎች በድረ-ገጻቸው ላይ አሏቸው?

# የሕግ ተወካይ ማግኘት

ከዚህ በታች ብቁ የሆነ የሕግ ተወካይ ለመፈለግ መሄድ የሚችሉባቸው ቦታዎች ዝርዝር አለ። ያስታውሱ፣ ከሕግ አማካሪ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ብታደርጉ፣ ምክር ለመስጠት ትክክለኛ መመዘኛዎች እንዳላቸው ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

- **የሕግ ማእከላት፡** የሕግ ማእከላት የሕግ ምክር፣ የ`ኬዝዎርክ` ፡ ውክልና ለግለሰቦች እና ቡድኖች ይሰጣሉ። ሁሉም የሕግ ማእከላት ነጻ ናቸው እና ለትርፍ መሰረት ያላደረገ ስራ ይሰራሉ። የአካባቢው ሰዎች በአስተዳደር ኮሚቴዎቻቸው ላይ እየሰሩ ተጠሪነታቸው ለአካባቢያቸው ይሆናል። ድረ-ገጻቸው የአካባቢ የሕግ ማዕከላትን እና የሚሸፍኑባቸውን የሕግ ዘርፎች ዝርዝር ያቀርባል። ሁሉም የሕግ ማእከላት የኢሚግሬሽን ምክር መስጠት አይችሉም። *https://www.lawcentres.org.uk/about-law-centres/law-centres-on-google-maps/alphabetically*

- **የሕግ ኣማካሪ ማግኘት፥** ከሕግ ማህበር የሕግ ኣማካሪ ማግኘት ነፃ አገልግሎት ነው። በSRA ስለሚተዳደሩ በእንግሊዝ እና በዌልስ ስላሉ ድርጅቶች ወይም ሰዎች መረጃ ይሰጣሉ። እያጋጠምዎ ባለው ችግር ወይም በቦታ ማፈላለግ ይችላሉ። *https://solicitors.lawsociety.org.uk*

- **የሕግ ድጋፍ ኣማካሪ ማግኘት:** እዚህጋ፣ በእንግሊዝ እና በዌልስ ውስጥ የሕግ እርዳታ ውል ያለው የህግ አማካሪ መፈለግ ይችላሉ። በምድብ ፍለጋ ለምሳሌ (ኢሚግሬሽን እና ጥገኝነት፣ መኖሪያ ቤት፣ የበጎ አድራጎት ጥቅማ ጥቅሞች፣ ዘመናዊ ባርነት) ኣጣርተው እና የፖስታ ኮድ፣ ወይም ከተማ ማስገባት ያስፈልግዎታል። https://find-legal-advice.justice.gov.uk

- **የአገልግሎት አቅራቢዎች ማውጫ፣** በሕግ ምደና ስለ ሕጋው ኢድጋፍ አቅራቢዎች መረጃ። ማውጫው የማህበረሰብ እንክብካቤን፣ አድልዎን፣ ቤተሰብን፣ መኖሪያ ቤትን፣ ኢሚግሬሽን እና ጥገኝነትን፣ ዘመናዊ ባርነትን፣ የህዝብ ህግን፣ የመንግስት ድጎማን፣ የአእምሮ ጤናን፣ ወንጀልን እና የእስር ቤት ህግን ያጠቃልላል። ማውጫው በየወሩ ይዘምናል። *https://www.gov.uk/government/publications/directory-of-legal-aid-providers*
- **ኣማካሪ ማግኘት**: ይህ መሰሪያ ስለ ጥቅማጥቅሞች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ስራዎች፣ የህግ ጉዳዮች እና ሌሎች ተግባራዊ እርዳታዎች የመረጃ ምንጮችን እና ምክሮችን ለመፈለግ ያስችልዎታል። *https://advicefinder.turn2us.org.uk*

# ከጠበቃዎ ጋር የመጀመርያ ግንኙነት

አንድ ጊዜ ጠበቃ ካገኙ በኋላ የመጀመሪያ ግንኙነትዎን ከእነሱ ጋር ይሆናል። ይህ በኢሜል፣ በጥሪ፣ በቪዲዮ ጥሪ ወይም በአካል በመገኘት በኩል ሊሆን ይችላል። በዚህ የመጀመሪያ ግንኙነት ወቅት ጉዳይዎን በተቻለ መጠን በዝርዝር ማስረዳት እና ያለዎትን ሁሉንም ማስረጃዎች ማሳየት በጣም ኣስፈላጊ ነው። ይህ ከሃገር ውስጥ ቢሮ ደብዳቤዎች ወይም ሰነዶች፣ ከዶክተሮች፣ ከቤተሰብ፣ ከአከባቢ ባለስልጣናት እና ከሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች የተፃፉ ደብዳቤዎች ወዘተ ሊያካትት ይችላል። እንደዚህ አይነት ማስረጃ ከሌለዎት ጉዳይዎ አይታይም ማለት አይደለም። ሆኖም አንዳንድ ደጋፊ ሰነዶች ካሉት ለጠበቃው በጣም ቀላል ይሆናል።

ጠበቃዎ፡ ጠበቃ ምን ማለት እንደሆነ፣ እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ እና እንደማይችሉ ያሉ ነገሮችን ማብራራት አለበት።

ምንም እንኳን ይህ በሂደቱ ገና የመጀመሪያ ደረጃ ቢሆንም፣ ጠበቃው አሁንም አንዳንድ የሕግ ምክር ወይም የሕግ መረጃዎችን ሊሰጥ ይችላል።

ጠበቃው እርስዎን በሕጋዊ መንገድ መወከል ማለት ለጠበቃው ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ አለባቸው እና `Client Authority Forum' የተባለ ቅጽ እንድትሞሉ ይጠይቅዎታል። ይህ ማለት እርስዎን በይፋ እንዲወክሉ ፈቃድ እየሰጧቸው ነው ማለት ነው። ጠበቃው የስኬት እድሎችዎ ምን ያህል ጠንካራ እንደሆኑ እና በእርስዎ ጉዳይ ላይ ሊመጡ የሚችሉ ማናቸውንም የግዜ ገደቦች በግልፅ እና በታማኝነት ማብራራት አለበት።

ከጠበቃ የተወሰነ የመጀመሪያ ምክር ስላገኙ ብቻ እርስዎን በይፋ ይወክላሉ ማለት አይደለም። ጠበቃው እርስዎን እየወከሉ እንደሆነ ከእርስዎ ጋር ግልጽ እንዲሆን መጠየቅ አለብዎት። ካልሆነ ግን እርስዎን የሚወክል ሌላ ጠበቃ መፈለግ አለብዎት።

ከጠበቃ ጋር ከመገናኘትዎ በፊት የመጀመርያ ምክር በነጻ መሆኑን ማረጋገጥ አለቦት ወይም ለመጀመርያ ምክክር መክፈል ይኖርቦታል።

ጠበቃው እርስዎን ካነጋገሩ በኋላ ጉዳይዎን እንደሚይዙት ሊወስኑ ይችላሉ። ይህ ማለት ጉዳይዎ ሊሳካ በሚችልበት ዕድል ኣይተው  እና ጠበቃው ስለሚመለከተው የሕግ ዘርፍ በቂ እውቀት ያለው ወይም የሌለው መሆኑ በማየት ይወሰናል።

አንዳንድ ጊዜ ጠበቃዎ ጉዳይዎ ሊሳካ እንደማይችል ወይም ምንም ኣማራጭ የለዎትም  ብሎ ሊወስን ይችላል። እንዲህ ከወሰነ፣ ጠበቃው ይህንን በጽሁፍ አስቀምጦ ለውሳኔያቸው ምክንያት መስጠን ይኖርባቸዋል።

ጠበቃዎ በመጀመሪያ ስብሰባዎ ውሳኔ መስጠት ላይችል ይሆናል። ማስረጃዎን ለማየት እና ውሳኔ ለማድረግ ጊዜ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ውሳኔ ሲያደርጉ በጽሁፍ ሊሰጡዎት ይገባል።

አንዳንድ ጊዜ ተጨማሪ መረጃ ሊፈልጉ ይችላሉ፣ ወይም የእርስዎን ሰነዶች እና ማስረጃዎች ለማየት ጊዜ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህን ካደረጉ በኋላ በጽሁፍ ምክር ሊሰጡዎት ይችላሉ።

# ከጠበቃዎ ጋር ያለዎት ግንኙነት

የሕግ ጠበቃዎ ጉዳይዎን ለመያዝ ኣንዴ ከተስማማ በኋላ ብዙ መረጃ ይሰጥዎታል እና በብዙ ነገሮች ላይ መስማማት አለብዎት። የተሰጠዎትን መረጃ ረጋ ብለው መረዳትዎን ኣረጋግጡ። እርግጠኛ ካልሆኑ ደግሞ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

ለርስዎ እና ለጠበቃዎ ታማኝ፣ ሙያዊ ግንኙነት-መመስረት አስፈላጊ ነው። ስለራስዎ ወይም አስቸጋሪ የሆነውን ያለፈው ታሪክዎን ለማጋራት መረጃ ማጋራት ሊኖርብዎ ይችላል። አሰቃቂ እና የማይመቹ ገጠመኞችን መግለጽ ሊኖርብዎ ይችላል፣ እና ጠበቃዎ ይህንን ምቹ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ኣኳሃን ውስጥ ማድረግ እንዲችሉ ለማረጋገጥ መስራት አለበት።

እርስዎ እና የሕግ ተወካይዎ ኣንድ ቡድን ነዎት፡ ለጉዳይዎ የተሻለውን ውጤት ለማግኘት አብረው መስራት አለብዎት። ለሁለታቹ ወገኖች መብቶች እና ግዴታዎች ያሉት ባለ ሁለት መንገድ ግንኙነት ነው።

## የደንበኛ ስልጣን ደብዳቤ

ጠበቃዎ የደንበኛ ስልጣን ደብዳቤ (Client Authority Letter) የሚባል ነገር እንዲፈርሙ ይጠይቅዎታል። ይህ ጠበቃው እርስዎን ወክሎ ለሆም ኦፊስ ወይም እርስዎን ወክሎ ሌሎች አካላትን እንዲያነጋግር ተፈቅዶለታል ማለት ነው። ይህን ከፈረሙ በኋላ ጠበቃው እርስዎን በይፋ ይወክላል።

## የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ

ጠበቃው ፋይል እየከፈትልዎ መሆኑን ለማረጋገጥ የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ሊልክልዎ ይገባል። 'ፋይል መክፈት' ማለት ጠበቃው በይፋ ጠበቃዎ መሆን እና ጉዳይዎን መያዙ ኣረጋግጧል ማለት ነው። ጠበቃዎ ፋይል ከከፈትልዎት በኋላ በሚቀጥለው ሁለት ሳምንታት ውስጥ የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ እንዲልክልዎት አስፈላጊ ነው።

የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ እነዚህን ማጠቃለል ኣለበት:

- ✓ የእርስዎ ደንበኛ ማጠቃሻ ቁጥር
- ✓ ስለ የኢሚግሬሽን ጉዳይዎ ዝርዝሮች
- ✓ የእርስዎን ጉዳይ እያስፈጸመ ያለው ሰው ዝርዝር ብቃቱን እና እውቅናውን ጫምር።
- ✓ መመሪያ፡ ለጠበቃው የሰጥዎት ስለ ሁኔታዎ ዝርዝር መምርያ።
- ✓ እስካሁን የተሰጠዎት ምክር ማጠቃለያ
- ✓ ለጉዳዩ የገንዘብ ድጋፍ መረጃ - የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ጉዳዩ በ ሕጋዊ ድጋፍ ድርጅት (LLA) ለሚሰጠው የሕግ እርዳታ ወይም ለየት ያለ የጉዳይ ፈንድ (LLA) እንዲደገፍ ብቁ መሆኑን መግለጽ አለበት።
- ✓ በእርስዎ ጉዳይ ጠበቃው ቀጥሎ የሚወስዳቸው እርምጃዎች በሚመለከት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡
    - ለሆም ኦፊስ የርእሰ ጉዳይ መዳረሻ ጥያቄ (SAR) ማድረግ። ይህ ማለት ሆም ኦፊስ ስለእርስዎ ያለውን መረጃ ሁሉ የሚጠየቅበት መንገድ ነው።
    - ስለጉዳይዎ መረጃ ለማግኘት ለቀድሞ ጠበቃዎችዎ ጥያቄ ማቅረብ
    - ሪፈራል ማድረግ (ወደ ሌላ ኣካል ማስተላለፍ)
    - ከሐኪምዎ የሕክምና መዝገብ (ሪኮርድ) መጠየቅ
- ✓ እንደ ደንበኛ ያለዎት ግዴታዎች። እነዚህም የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡
    - ሁኔታዎ በማንኛውም መንገድ ከተቀየረ እነሱን ማሳወቅ
    - እንደአስፈላጊነቱ ስለገንዘብ ሁኔታዎ መረጃ እና ማስረጃ መስጠት
    - እንደአስፈላጊነቱ ከጓደኞች፣ ከደጋፊ ሰራተኞች ወይም ከማህበራዊ ሰራተኞች የድጋፍ ደብዳቤ ለማግኘት መሞከር

- ለጉዳይዎ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ማቅረብ፡ ይህም ስለ ቤተሰብዎ ስለ ልጆችዎ ወዘተ ያጠቃልላል።

✓ የስኬት እድሎች፡- ይህ ጉዳይዎ ምን ያህል ሊሳካ እንደሚችል ለመረዳት እንዲረዳዎት ነው።

✓ የጊዜ መጠን፡- ይህ ሂደት ጊዜን በተመለከተ ግንዛቤን ይሰጣል። ሆኖም፣ እባክዎን አንድ ጉዳይ ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ለመገመት አስቸጋሪ እንደሚሆን ያስታውሱ

✓ መረጃ ስለ የርስዎን ጉዳይ የሚቆጣጠረው ማን እንደሆነ እና የህግ አማካሪዎ በሚሰጠው አገልግሎት ደስተኛ ካልሆኑ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ።

ደብዳቤው በጠበቃው ኦፊሴላዊ ወረቀት ላይ መጻፍ አለበት። ግልጽ፣ አጭር እና አስፈላጊ መረጃን ያካተተ መሆን አለበት።

ጠበቃ ጉዳይዎ ሊሳካ እንደማይችል ካመነ ወይም በሕጉ መሰረት ጉዳይዎ የሚያሸንፍበት ምንም አይነት መንገድ ከሌለ ይህንን በደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ሊጽፉላችሁ ይችላሉ። ይህ ውስኔ ጉዳይዎን በዝርዝር ከተመለከቱ በኋላ ብቻ መወሰን አለባቸው።

# ከጠበቆች ጋር መስራት

## ከጠበቃ ምን መጠበቅ እንደሚችሉ?

- **ግልጽነት**: ይህ ማለት የሕግ ተወካዩ ስለሚሰጡት አገልግሎት እያንዳንዱ ክፍል ለእርስዎ ሁልግዜ ግልጽ መሆን አለበት ማለት ነው።
- **ጥራት፥** ቴክኒካዊ ህጋዊ ቋንቋን ከመጠቀም መቆጠብ አለባቸው እንዲሁም የሚነግሩዎትን ነገር መረዳትዎን ማረጋገጥ አለባቸው።
- **ተደራሽነት**: ሂደቱ እንዴት እንደሚሰራ እና በእርስዎ ጉዳይ ላይ ምን እየሆነ እንዳለ በየጊዜው ሊያሳውቁዎት ይገባል።
- **ክፍትነት**: ከጠበቃዎ ጋር በሐቀኝነት ለመናገር ምቾት ሊሰማዎት ይገባል።በድርጊታቸው ካልተስማማህ ወይም የሆነ ነገር ካልገባዎት ለመናገር ነፃነት ይሰማዎ። ጥያቄዎችን የመጠየቅ እና ሂደቱን የመረዳት መብት አልዎት።
- **ማስተናገድ**: ጠበቆች ደንበኞቻቸው ሁሉ በሂደቱ ውስጥ መሳተፍ መቻላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸውን የሚነኩ የአካል ጉዳት አለባቸው፣ እና ሁሉም የአካል ጉዳት ሊታይ አይችልም። የህግ ተወካዮች ፍላጎቶችዎን እና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተረድተው እርስዎን ለማስተናገድ ጥረት ማድረግ አለባቸው።
- **ታማኝነት**: ሁሉም ሰው ጠበቃውን ማመን እንደሚችል ሊሰማው ይገባል።

ጠበቃዎ ማናቸውንም የግዜ ገደቦች ወይም አስፈላጊ ቀናት መግለጽ አለበት። ምንም እንኳን እርስዎን ለመርዳት ምንም ማድረግ ባይችሉም ፣ እርስዎ ሊወስዷቸው የሚችሏቸውን ቀጣይ እርምጃዎች ማወቅዎን ማረጋገጥ አለባቸው።

ሁሉም ማስረጃ ከእርስዎ መገኘት የለበትም። ጠበቆች አንዳንድ ማስረጃዎችን በማዘጋጀት ሊረዱ ይችላሉ፣ ለምሳሌ የባለሙያ ማስረጃ ከዶክተር ስለ የጤና፡ ወይም ስለ ትውልድ ሀገርዎ ሁኔታ ላይ ከአንድ አዋቂ ከሆነ ሰው ማስረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## ጠበቃ ከእርስዎ ምን ይጠብቃል?

- **ታማኝነት**: የሕግ ተወካዮች ሁኔታዎን በሐቀኝነት እንድታብራሩላቸው ይጠብቃሉ፥ ለምሳሌ፥ ስለ ገንዘብ ነክ ሁኔታዎችዎ፣ ስለ አካላዊ እና አእምሮአዊ ጤንነትዎ፣ ስለ ማንኛውም የአካል ጉዳት ካልዎት ወዘተ እንድትነግሯቸው። ጠበቃው እውነተኛውን ሁኔታ ካላወቀ፣ እርስዎ በሚያገኙትን ምክር እና ጠበቃው እርስዎን ወክሎ ሊወስዳቸው የሚችላቸውን እርምጃዎች ላይ ተጽእኖ ልያሳርፍ ይችላል።

- **ተሳትፎ**: ከሂደቱ ጋር መሳተፍ ያስፈልግዎታል። ይህ ማለት በቀጠሮ መገኘት፣ ስልክዎን መመለስ፣ ሰነዶችን ማቅረብ እና የመሳሰሉትን ነገር ማድረግ ማለት ነው።
- **ትብብር**: የሕግ ተወካዮች ብዙውን ጊዜ በጠባብ ቀነ-ገደቦችን ነው የሚሰሩት፣ እና ሰነዶችን በሰዓቱ እንዲያቀርቡ እንድትተባበርዋቸው ይፈልጋሉ። አንዳንድ ጊዜ መረጃ እንዲሰጧቸው፣ ሰነዶች እንዲፈርሙ ወይም በአጭር ማስታወቂያ ማስረጃ እንድታቀርቡላቸው ይፈልጋሉ። እርስዎን ለመርዳት እንዲችሉ የእርስዎን እርዳታ ይፈልጋሉ።

በእርስዎ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሰዎች ሊሳተፉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ዋናው መረጃ በዋናነት ከእርስዎ መምጣት አለበት። ጠበቆች ምንም ነገር መገመት ወይም ከማንም ሌላ ሰው መመሪያ መውሰድ አይችሉም።

## የደንበኛ-ጠበቃ ግንኙነት - አጠቃላይ መመሪያዎች

1. የተለያዩ አስተያየቶችን የመጠየቅ መብት አለዎት። ሆኖም፣ ሐቀኛ መሆን አለበት እና የተለያዩ ጠበቆችን በተመሳሳይ ጊዜ ለተለያዩ ማመልከቻዎች መጠቀም የለበትም። ይህ ጊዜ የሚወስድ እና የጉዳይዎን ሂደት በእጅጉ ሊጎዳ ይችላል።

2. ጠበቆች ማስረጃ ለመሰብሰብ መሞከር የምትችሉባቸው መንገዶች ሊጠቁሙ ይችላሉ። ይህን ማድረግ ከባድ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፣ የድሮ ኢሜይል ማግኘት ወይም በአሁኑ ሰዓት ምንም ግንኙነት ከሌላችሁ ሰው ጋር መነጋገር)፣ ነገር ግን ጠበቃዎ የሚፈልገውን ሁሉንም ማስረጃ ለማግኘት የተቻለዎትን ሁሉ ማድረግ አለብዎት።

3. የአስተርጓሚ ሚና መተርጎም ብቻ ነው። የህግ ምክር መስጠት አይችሉም። እርስዎ የሚሉትን ወደ ሕጋዊ ወኪሉ ቃል በቃል መተርጎም አለባቸው። እንዲሁም የሕግ ተወካዩ የሚላችሁን ቃል በቃል ለእርስዎ መተርጎም አለባቸው።

4. ጠበቃ የሚያስፈልገው ሊመራዎት እና ሊያማክርዎት ነው። እና የትኛው የስደተኛ ሕግ ነው ለእርስዎ ጉዳይ ሆም ኦፊስ መሰረት የሚያረገው እንዲነግርዎት ነው። ለሆም ኦፊስ ምን እንደሚሉ ሊነግሩዎት አይችሉም።

5. ሁሉንም ከሆም ኦፊስ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን በህጋዊ ተወካይዎ በኩል መሆን የተሻለ ነው

6. እያንዳንዱ ሰው ልዩ ነው, ስለዚህ እያንዳንዱ ጉዳይ የተለየ ይሆናል። የሆም ኦፊስ ሕጎች አንዳንድ ጊዜ እንደ ሰዎች ልዩ ሁኔታ ለተለያዩ ጉዳዮች በተለያየ መንገድ ሊሰራ ይችላል። ለዚያም ነው ጉዳይዎን ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለማወዳደር መሞከር ያለብዎት፡ ይህ አላስፈላጊ ጭንቀት እና ውጥረት ሊፈጥር ይችላል።

## ከሕግ ወኪልዎ ጋር ደስተኛ ካልሆኑ ምን ማድድረግ እንዳለብዎ

የሕግ ተወካይዎ በሰጡት አገልግሎት ካልረኩ፣ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። ቅሬታ ሊያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጥቂት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ከፍተኛ የኮሙኒኬሽን እጥረት**: ለምሳሌ፣ የሕግ ተወካይዎን ለማግኘት ሲሞክሩ ምላሽ ሳያገኙ ለረጅም ጊዜ (ብዙ ሳምንታት ወይም ወራት) ከቆዩ።

- የሕግ ተወካዩ ስላደረጉት ወይም ስላላደረጉት ነገር ባይነግርዎት።

- የህግ ተወካይዎ ከፍላጎትዎ ውጪ እርምጃ ወስዷል።

- ያለምንም ማብራሪያ ከተስማሙበት በላይ ገንዘብ ኣስከፍልዎታል።

- የርስዎ ጉዳይ ለረጅም ጊዜ ዘግይቷል ምክንያቱም የህግ ተወካይዎ እናደርጋለን ያሉትን ስላላደረጉ።

- ሰነዶችዎን አጥፍተውታል።

- የማይጠቅም ምክር ሰጥተዎታል - ለምሳሌ፣ ኣንድ ነገር ነግረዎት በኋላ ትክክል ኣለመሆኑን ኣወቁት።

ስለ ህጋዊ ተወካይዎ ቅሬታ ማሰማት ከፈለጉ፣ ከገለልተኛ ድርጅት ድጋፍ ከማግኘታችሁ በፊት በመጀመሪያ ቅሬታዎን ለኣማካሪው ማቅረብ አለብዎት። ስለጉዳይዎ የሚያሳስብዎት ነገር ካለ በመጀመሪያ ስጋቶችዎን መፍታት ይችሉ እንደሆነ ለማየት ከህጋዊ ተወካይዎ ጋር በቀጥታ መነጋገር አለቦት። በዚህ ካልተፈታ ወደ የህጋዊ ተወካይዎ ተቆጣጣሪ እንዲተላለፉ መጠየቅ ይችላሉ። በሂደቱ መጀመሪያ ላይ በተሰጡዎት የደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ላይ የተቆጣጣሪው ስም መኖር አለበት።

እንደ አማራጭ፣ ቅሬታዎን በድርጅቱ ውስጥ ለሚመለከተው ሰው ቅሬታዎን ማቅረብ ይችላሉ። ስማቸው በደንበኛ እንክብካቤ ደብዳቤ ላይም መኖር አለበት። ድርጅቱ የሚያሳስብዎትን ጉዳይ እንደሚመለከቱት በጽሁፍ ምላሽ ሊሰጥዎ ይገባል።

ብዙውን ጊዜ ከውጭ ድርጅቶች እርዳታ ከመጠየቅዎ በፊት ቅሬታዎ ለአማካሪው ማቅረብ አለብዎት። የህግ ተወካይ ወይም ድርጅታቸው ቅሬታዎን እንዴት እንዳስተናገዱ ካልረኩ፣ **የህግ እንባ ጠባቂን** መጠየቅ ይችላሉ፡-

[https://www.legalombudsman.org.uk](https://www.legalombudsman.org.uk)

የሕግ እንባ ጠባቂ ደካማ አገልግሎትን የሚመለከት ገለልተኛ አካል ነው። ቅሬታ ያልዎት ድርጅት ላይ ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ ገንዘብ እንዲመልስ ወይም ህጋዊ ክፍያዎችን እንዲቀንስ ወይም ድርጅቱ ካሳ እንዲከፍልዎት ማዘዝ ይችላል። የሕግ እንባ ጠባቂ ነጻ እና ገለልተኛ ነው።

ስለተቀበሉት አገልግሎት ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልግዎታል። ስለ ጠበቆች፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የጠበቆች ወጪ፣ የሕግ አስፈጻሚዎች ወዘተ ቅሬታዎችን መመርመር ይችላሉ። የእነርሱ ድረ-ገጽ የሚመረምሩትን ቅሬታዎችና የሚሰጡትን ድጋፍ ምሳሌዎች አሉት፡-

[https://www.legalombudsman.org.uk/information-centre/case-studies](https://www.legalombudsman.org.uk/information-centre/case-studies)

ለህጋዊ እንባ ጠባቂ ቅሬታ ለማቅረብ በድህረ ገጻቸው ገብተው ወደ የቅሬታ ማቅረቢያ ገጽ ይሂዱ፡

[https://www.legalombudsman.org.uk/make-a-complain](https://www.legalombudsman.org.uk/make-a-complain)

# ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እና ማእከላት

| ድርጅት | ኣገልግሎት |
|---|---|
| **ኣፍሪካ ረፊዩጂ ኮሙኒቲ**<br><br>**የሚያገለግሉበት ኣካባቢ:** ለንደን ቦሮ ባርነት እና ካምደን<br><br>**ስልክ:** 020 8368 9070 / 0795 656 6573<br><br>**ኢመይል:** africanrefugeecommunity@acrc.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ:** https://www.africanrefugeecommunity.co.uk | **የሚሰጡበት ኣገልግሎት:** ለፈረንሳይ፣ ሊንጋላ፣ ኪኮንጎ እና ስዋሂሊ ተናጋሪ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ምክር እና መረጃ ይሰጣሉ። የሚሸፈኑ ጉዳዮች ደግሞ የኢሚግሬሽን፣ የመኖሪያ ቤት፣ የበጎ አድራጎት ጥቅማ ጥቅሞች፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ደህንነት እና ስራን ያካትታሉ። በሲቪ ዝግጅት ላይ እገዛ ያደርጋሉ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች:** ፈረንሳይኛ፣ ሊንጋላ፣ ኪኮንጎ እና ስዋሂሊ ተናጋሪ ስደተኞች እና ከአፍሪካ ጥገኝነት የሚጠይቁ ሰዎች። |
| **የጥገኝነት እርዳታ (የሄለን ባምበር ፋውንዴሽን ቡድን አካል)**<br><br>**ስልክ:** 020 7354 9631<br><br>**ኢመይል**: advice@asylumaid.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://asylumaid.org.uk | **የሚሰጠው ኣገልግሎት:** በዩኬ ውስጥ ጥገኝነት ለሚጠይቁ ሰዎች የህግ ውክልና መስጠት፡ ስለ ልጆች፣ ስለ ከህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች የዳኑ ሰዎች እና ስለ ሀገር አልባ ሰዎች። |
| **ስለ ኢሚግሬሽን እስረኞች ዋስትና**<br><br>**ኣገልግሎት የሚሰጥበት ኣካባቢ:** ኢንግላንድ፡ ስኮትላንድ፡ እና ወልስ<br><br>ስልክ: 020 7456 9750<br><br>**ኢመይል:** enquiries@biduk.org<br><br>**ድረ-ገጽ:** https://www.biduk.org | **የሚሰጠው ኣገልግሎት:** በእስር ወይም በመቆያ ማእከል ውስጥ በኢሚግሬሽን ሥልጣን ተይዘው ለሚገኙ ስደተኞች ስለ ዋስትና እና ከአገር ስለመባረር ጉዳይ የሕግ ምክር እና መረጃ ይሰጣሉ። በጣም ተጋላጭ ለሆኑ እስረኞች የተወሰነ ውክልና ስለ ዋስትና ማመልከቻዎች ይሰጣሉ። በመላው ዩናይትድ ኪንግደም የሚገኙ እስር ቤቶች እና የመቆያ ማእከላት ይሸፍናሉ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች:** በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ የኢሚግሬሽን ቁጥጥር የሚደረግበት እና በስደተኞች ባለስልጣን  በእስር ቤቶች እና በማቆያ ማእከላት ውስጥ የሚታሰር ማንኛውም ሰው ይመለከታል። |
| **የብሪጣንያ ቀይ መስቀል-ለንደን የስደተኞች ድጋፍ ቡድን**<br><br>**Phone:** 020 7704 5670 | **የሚሰጠው ኣገልግሎት፡** ለጥገኝነት ጠያቂዎች እና ለስደተኞች ጉዳይ ስራዎች የጥገኝነት ድጋፍን፣ የበጎ አድራጎትና የማህበራዊ ጥቅማ ጥቅሞችን፣ የመኖሪያ ቤቶችን እና የማህበረሰብ እንክብካቤን ጨምሮ በማህበራዊ ደህንነት መብቶች ላይ ምክር ይሰጣሉ። |

| | |
|---|---|
| **Website:** https://www.redcross.org.uk | የኢሚግሬሽን ምክር እና የካውንስሊንግ አገልግሎትም ይሰጣሉ |
| **ካርዲናል ህዩም ማእከል**<br><br>**ስልክ**: 020 7227 1673<br><br>**ኢሜይል**: info@cardinalhumecentre.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://www.cardinalhumecentre.org.uk | **የሚሰጠው አገልግሎት**: የኢሚግሬሽን ምክር፣ የማህበራዊ ጥቅማ- ጥቅሞች እና መኖሪያ ቤት፣ ሥራ እና ለአዋቂዎች ትምህርት ይሰጣሉ |
| **ኮሙኒቲ አክሽን ለ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች (CARAS)**<br><br>**የሚያገለግሉበት አካባቢ: ሳውዝ ኢስት ለንደን**<br><br>**ስልክ**: 020 8767 5378<br><br>**ኢሜይል:** info@caras.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ: https://caras.org.uk/contact** | **የሚሰጠው አገልግሎት**: በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎች የእንግሊዝኛ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣ አገልግሎቶችን እና እድሎችን እንዲያገኙ፣ ደጋፊ ማህበራዊ አውታረ መረቦችን እንዲገነቡ እና የቅቡልነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚደግፉ የተለያዩ የቡድን እንቅስቃሴዎች አሏቸው። ሰዎች ምንም ያህል ውስብስብ ጉዳይ ቢኖራቸውም ከሁኔታቸው ጋር የሚስማማ ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ ከግለሰቦች ጋር ይሰራሉ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች |
| **ኮሙኒቲ አድቫይዝ ፕሮግራም ኢሊንግ**<br><br>**የሚያገለግሉበት አካባቢ፥ ለንደን ቦሮ ኢሊንግ**<br><br>**ተለፎን:** 020 8231 2575 / 020 8231 2576 / 020 8231 2550 / 0208 231 2574<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://www.wlec.net/cap | **የሚሰጡት አገልግሎት፥** ምክር እና መረጃ ለአካባቢው ማህበረሰብ ስለ መኖሪያ ቤት፣ ማህበራዊ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ሥራ ስምሪት፣ ኢሚግሬሽን፣ ዕዳ እና የሸማቾች ጉዳዮች። አስፈላጊ ከሆነ ወደ ልዩ ባለሙያተኛ ለምክር ይልካሉ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: የአካባቢው ማህበረሰብ. |
| **ዲተንሽን አክሽን**<br><br>**ያሚያገለግሉበት አካባቢ**: ኢንግላንድ እና ወልስ<br><br>**ስልክ**: 0800 587 2096 (ለእስረኞች ነጻ ነው) / 020 7226 3114 (ቢሮ)<br><br>**ኢሜይል:** casework@detentionaction.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://detentionaction.org.uk | **የሚሰጡት አገልግሎት**: በኮለንብሩክ እና በሃርመንድስዎርዝ የኢሚግሬሽን ማስወገጃ ማእከላት ለታሰሩ ወይም በማቆያ ማእከላት ውስጥ በኢሚግሬሽን ባለስልጣን ለታሰሩ ሰዎች ተግባራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ ይሰጣሉ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: በማቆያ ማእከላት እና እስርቤቶች በኢሚግረሽን ለታሰሩ |

| | |
|---|---|
| **የኤርትራ ኮሙኒቲ በዩኬ**<br><br>**የሚሸፍናቸው ኣካባቢዎች**: በ ዩኬ ውስጥ ላሉ ኤርትራውያን በሙሉ እና - በዋነኛነት በእዝሊንግተን፣ ሃሪንገ፣ ካምደን እና ሃክኒ ይሰራል<br><br>ስልክ: 020 7700 7995 / 0795 116 4558 / 0794 737 3266<br><br>**ኢመይል**: office@ericomuk.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: http://www.ericomuk.org.uk | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: ለኤርትራ ማህበረሰብ፣ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ጨምሮ ምክር እና መረጃ ይሰጣል። በነፊት፣ ኢሚግሬሽን፣ መኖሪያ ቤቶችን፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችን፣ ስልጠናን፣ የቤተሰብ ጉዳዮችን እና ትምህርትን፣ የንግድ ስራን ማዋቀርን ያካትታሉ። ለሴቶች እና ለአረጋውያን የድጋፍ ቡድኖች።የድጋፍ ትምህርት ቤቶች፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ክፍሎች፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: የኤርትራ ማህበረሰብ፥ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች። |
| **ሃክሚ ማይግራንት ሰንተር**<br><br>**ኢመይል:** info@hackneymigrantcentre.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ:** **https://hackneymigrantcentre.org.uk** | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: ነጻ፣ ሳምንታዊ የምክር እና የድጋፍ አገልግሎት ለአደጋ ተጋላጭ ስደተኞች በስደተኝነት ጉዳይ፣ ስለ መኖሪያ ቤት፣ ደህንነት እና የጤና ተደራሽነት። ሃክኒ ማይግራንት ሰንተር የ OISC እውቅና ተሰጥቶታል። እንዲሁም ለሁሉም ጎብኚዎች የበሰለ/የተቀቀለ ምግብ ይሰጣሉ.<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ሁሉም ስደተኞች፣ የስደት ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምንም ፣ ስለ ዜግነት ወይም የመኖሪያ ቦታ በሚመለከት ጉዳይ። |
| **ሃሪንገ ማይግራንት ሳፖርት ሰንተር**<br><br>**ስልክ:** 020 4566 7412 / 020 4566 7445<br><br>**ኢመይል:** info@haringeymsc.org<br><br>**ደረ-ገጽ:** http://haringeymsc.org | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: ከህግ ባለሙያዎች ለስደተኞች ነፃ የኢሚግሬሽን ምክር ለሚሰጡ ሳምንታዊ አገልግሎት፣ እና ምክር፣ የተወሰነ ከይዝዎርክ እና ማህበራዊ እንክብካቤ (ለምሳሌ ዓንቀጽ 17 እና የአዋቂዎች ማህበራዊ እንክብካቤ) እና የመኖሪያ ቤት ጉዳዮችን ኣገልግሎት ይሰጣል። እንዲሁም የጤና ምክር፣ የኤን ኤች ኤስ (NHS) አገልግሎቶችን ማግኘት እና ትኩስ ምግብን በማቅረብ እገዛን ይሰጣል።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ጨምር |
| **IMECE የሴቶች ማእከል**<br><br>**የሚሸፍናቸው ኣካባቢዎች**: ለንደን በሙሉ<br><br>**ህዝባዊ ተለፎን**: 020 7354 1359 / 020 3227 3592<br><br>**ኢመይል**: info@imece.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: **http://www.imece.org.uk** | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: ስለ ስደት ጉዳይ፣ ዘበታዊ-ዓመጽ፥ ስለ መኖሪያ ቤት፣ በነፊት፣ ጤና እና በትምህርት፥ ዙሪያ የምክር እና የድጋፍ አገልግሎቶች። የጤና ሴሚናሮች እና አንዳንድ ማህበራዊ ዝግጅቶች፡ የአእምሮ ጤና ፕሮጀክት (ካውንስሊንግ) እና የችግር ጣልቃገብነት ኣገልግሎት ይሰጣሉ። ማዳረስ(outreach)። ዘቤታዊ ዓመጽ፥ አቅም ግንባታ፥ የስልክ ምክር። |

| | |
|---|---|
| | **ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ቱርካውያን፣ ቱርካውያን እና ሲፕሪዮት፡ ቱርካውያን ሴቶች እና ሌሎች ቱርክ ተናጋሪ ሴቶች |
| **ኢንዶአመሪካን ስደተኞች ድርጅት (IRMO)**<br><br>**የሚሸፍናቸው አካባቢዎች**: ለንደን (ሁሉም በሮዎች).<br><br>**ኢመይል**: mail@irmo.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: http://irmo.org.uk | **የሚሰጡት አገልግሎት**: አራት ቁልፍ በታዎችን የሚያካትት ሁሉን አቀፍ አቀራረብን ይሰጣሉ፡-ምክር እና ማህበራዊ እንክብካቤ፣ ትምህርት፣ ስልጠና እና ሥራ፣ ልጆች፣ ወጣቶች እና ማህበረሰብ። በኢሚግሬሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የመቋቋሚያ እቅድ ድጋፍ እና በማህበራዊ እንክብካቤ፣ መኖሪያ ቤት እና ታክስ ጉዳይ ላይ ምክር እንሰጣለን። ለአዋቂዎች የእንግሊዝኛ ትምህርት፣ የግንባታ ማሰልጠኛ ኮርሶች (CSCS ካርድ) እና ለአዋቂዎች የስራ ድጋፍ እና መካሪ እናቀርባለን።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ላቲንግ አመሪካን (እስፓንያ እና ፖርቱጋል ቋንቋ ተናጋሪዎች) ስደተኞች |
| **ኢዝሊንተን ረፊዩጂ ፎረም**<br><br>**የሚሸፍናቸው አካባቢዎች**: ለንደን በሮ ኢዝሊንግተን<br><br>**ስልክ**: 020 7832 5847<br><br>**ኢመይል**: info@islingtonrefugeeforum.org<br><br>**ድረ-ገጽ**: http://islingtonrefugeeforum.org/contact-islington-refugee-forum | **Service offered:** በስደተኞች የሚመራ መድረክ ሆኖ በእዝሊንግተን የስደተኞችን የህይወት ለማሻሻል ያለመ ነው። የስደተኞች ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ የስደተኞች አገልግሎቶችን፣ የስደተኞች አገልግሎት የሚሰጡ ዋና ድርጅቶችን እና ከስደተኞች ጋር የሚሰሩ ስፔሻሊስት ግለሰቦች በማሰባሰብ ይረዳሉ። .<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: የስደተኞች ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ሌሎች ኤጀንሲዎች እና ግለሰቦች ከስደተኞች ጋር የሚሰሩ። |
| **ጀስዊት ረፉጂ ሰርቪስ**<br><br>**የሚሸፍናቸው አካባቢዎች**: ለንደን<br><br>**ስልክ**: 020 7488 7310<br><br>**ኢመይል**: uk@jrs.net<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://www.jrsuk.net | **የሚሰጡት አገልግሎት**: JRS UK በሄትሮው እና በኮልብሮክ ማቆያ ማእከላት ውስጥ ላሉ ሰዎች እና ለእስር ለነበሩ ሰዎች የአቻ ድጋፍ ቡድን ያቀርባል። JRS UK በአገልግሎታችን ለተመዘገቡ ድሆች ጥገኝነት ጠያቂዎች ምክር እና የስራ ጉዳይ፣ የተግባር ድጋፍ፣ የፈጠራ እና የጤና ተግባራት፣ ትንሽ የማስተናገጃ እቅድ እና ልዩ የህግ ምክር አገልግሎትም ጭምር አጠቃላይ ድጋፍን ይሰጣል።<br><br>**ትኩረት የሚደርግላቸው ግሩፖች**: በእስር ላይ ያሉ፣ ቀደም ሲል ታስረው የነበሩ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ወይም በጣም የተቸገሩ ስደተኞችን ይርዳሉ። |

| | |
|---|---|
| **ልዊሻም ረፊዩጂ ኣንድ ማይግራንት ሄልፕላይን**<br>**Lewisham Refugee and Migrant helpline**<br>**ስልክ:** 020 8694 0323<br><br>**ኢመይ:** info@lrmn.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ:** https://www.lrmn.org.uk | **የሚሰጡት ኣገልግሎት:** ምክር እና መረጃ ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ይሰጣል። ስለ ኢሚግሬሽን፣ የመኖሪያ ቤት እና የማህበራዊ እንክብካቤ እና ጾታዊ ጥቃትን በተመለከተ ምክር ይሰጣሉ። እንዲሁም የአንድ ለአንድ ምክር (ካውንስሊንግ) ይሰጣሉ። ስለ ሥራ እና ስልጠና ምክር ይሰጣሉ ፣ ምክር እና ድጋፍ ለልጆች እና ወጣቶች እንዲሁም የሉዊሻም ነዋሪዎችን የአእምሮ ጤንነት በሚመለከት ጉዳይ የሚያማክር ቡድን ኣላቸው።<br><br>**ቱክረት የሚደረግላቸው ግሩፖች:** ስደተኞች፣ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ በተለይም ጾታዊ ጥቃት ያጋጠማቸው። |
| **ማይግራንትስ ኦርጋናይዝ**<br>**Migrants Organise**<br>ስልክ: **020 8964 4815**<br>**ኢመይል:** info@migrantsorganise.org<br><br>**ድረ-ገጽ:**<br>https://www.migrantsorganise.org/community-programme | **የሚሰጡት ኣገልግሎት:** የማህበረሰባቸው ፕሮግራም ደህንነቱ የተጠበቀ እና እንግዳ ተቀባይ አካባቢን የሚፈጥሩ የምክር፣ የጥብቅና፣ የስልጠና፣ የምክር እና የቡድን እንቅስቃሴ በሚመለከቱ ጉዳዮች ይሰራሉ። ስለ ኢሚግሬሽን፣ የጥገኝነት ድጋፍ፣ የማህበራዊ ድጎማ፣ የመኖሪያ ቤት እና የማህበረሰብ እንክብካቤ ላይ ምክር ይሰጣሉ።<br><br>**ቱክረት የሚደረግላቸው ግሩፖች:** ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ። |
| **ኖትረዳም ረፉጂ ሰንተር**<br><br>**Notre Dame Refugee Centre**<br><br>**የሚሸፍኑት ኣካባቢ:** London<br><br>**ኢመይል:** info@notredamerc.org.uk<br><br>**ህዝባዊ ስልክ:** 020 7388 8198<br><br>**ድረ-ገጽ:**<br>**https://www.notredamerc.org.uk** | **የሚሰጡት ኣገልግሎት:** ስለ ኢሚግሬሽን እና የጥገኝነት ማመልከቻዎች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ማህበራዊ ድጎማ እና የማህበራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት በስልክ መስመር ምክር ይሰጣሉ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው:** ስደተኞች ኣና ጥገኝነት ጠያቂዎች |
| **ፕራልስስ - Praxis**<br><br>**ስልክ:** 020 7729 7985<br><br>**ፋክስ:** 020 7729 0134<br><br>ከኣማካሪ ጋር ለመነጋገር ይህን ደውሉ<br><br>020 7749 7608 or 020 7749 7605<br><br>**ድረ-ገጽ:** https://www.praxis.org.uk | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: በዩኬ ውስጥ ላሉ ስደተኞች የባለሙያ ድጋፍ ይሰጣሉ። የኢሚግሬሽን እና የመኖሪያ ቤት ምክር ይሰጣሉ። ቤት እጦት ለሚገጥማቸው ስደተኞች ድጋፍ፣ እንዲሁም ከህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች የዳኑ እና ዘቤታዊ ያጋጠማቸው ሰዎች፣ ወጣቶች፣ የአውሮፓ ህብረት ዜጎች እና የረጅም ጊዜ ነዋሪዎች የሚፈልጉትን ድጋፍ ለማግኘት እየታገሉ ላሉ ሰዎች ድጋፍ ይሰጣል። |
| **ረይንቦው ማይግረሽን** | **የሚሰጡት ኣገልግሎት:** ለራስ ግምት ከፍታ መጨመር እና በራስ መተማመንን ለማሻሻል፣ መገለልን ለመቀነስ እና |

| | |
|---|---|
| **Rainbow Migration**<br><br>ስልክ: 020 7922 7811<br><br>**ኢሜይል**: hello@rainbowmigration.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://www.rainbowmigration.org.uk | የጤና አገልግሎቶችን እና መኖሪያ ቤቶችን ለማግኘት የሚረዳ ተግባራዊ እና ስሜታዊ ድጋፍ ይሰጣል። ጥገኝነት ለሚጠይቁ ወይም ከአጋሮቻቸው ጋር በእንግሊዝ ኣገር ለመኖር የአጋርነት ማመልከቻ ለሚያደርጉ LGBTQI+ ሰዎች የልዩ ባለሙያ የህግ መረጃ እና ምክር ይሰጣሉ። ሰዎች ጥራት ያለው የህግ ውክልና ለማግኘት ከብዙ የህግ ድርጅቶች ጋር ሽርክና አላቸው።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: LGBTQI+ እና ጥገኝነት ለሚጠይቂ ሰዎች |
| **ረኒዋል ፕሮግራም ሊሚትድ፡ ረፊዩጂና ማይግሬንት ፕሮጀችት (RAMP)**<br><br>**Renewal Programme Ltd.'s Refugee and Migrant Project (RAMP)**<br><br>**ስልክ**: 020 8471 6954<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://www.renewalprogramme.org.uk | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: Advice and support for refugees, asylum seekers and migrants on benefits and housing. Support for people with no recourse to public funds, including food parcels and second-hand clothes.<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ስደተኞች፥ ጥገኝነት ጠያቂዎች እና የመሳሰሉት |
| **የሴቶች መብት**<br><br>**Rights of Women**<br><br>**የሚሸፍኑት ኣካባቢ**: ኢንግላንድ እና ወልስ<br><br>**ስልክ**: 020 7251 6577 (የቤተሰብ ሕግ የምክር መስመር)<br><br>**ኢሜይል**: casework@detentionaction.org.uk<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://rightsofwomen.org.uk | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: ሁሉም የምክር መስመሮች በተለያየ ጊዜ ይከፈታሉ ፡ የቤተሰብ ሕግ ምክር በ2 የተለያዩ የስልክ መስመሮች፣ የወንጀል ምክር በሌላ መስመር፣ የኢሚግሬሽን እና የጥገኝነት ምክር (በዋና የኢሚግሬሽን መስመር ደግሞ፣ የአውሮፓ ህብረት የሰፈራ እቅድ፣ የባለሙያዎች ምክር መስመር) እና በስራ ገበታ ላይ ለሚያጋጥሙ ወሲባዊ ትንኮሳ።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ሴቶች |
| **ሳዘክ ደይ ሰንተር ለጥገኝነት ጠያቆዎች**<br><br>**Southwark Day Centre for Asylum Seekers**<br><br>**የሚሸፍኑት ኣካባቢ**: ለንደን ሳዘክ<br><br>**ኢሜይል**: office@sdcas.org.uk<br><br>**ህዝባዊ ስልክ**: 020 7732 0505<br><br>**ድረ-ገጽ**: https://www.sdcas.org.uk | **የሚሰጡት ኣገልግሎት**: በአጠቃላይ ምክር እና እርዳታ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት ለማመቻቸት ተስፋ እናደርጋለን፣ በተለይም በጤና፣ መኖሪያ ቤት፣ ስራ፣ ስልጠና፣ ትምህርት እና የጥገኝነት ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን።<br><br>**ትኩረት የሚደረግላቸው ግሩፖች**: ስደተኞች እና ጥገኝነት የሚጠይቁ ሰዎች በሳዘክ የለንደን በሮው። |

THE JOINT COUNCIL *for* THE WELFARE OF IMMIGRANTS

JCWI ከ1967 ጀምሮ በኢሚግሬሽን፣ በዜግነት እና በጥገኝነት ፖሊሲ ጉዳይ ለፍትህ እና ፍትሃዊነት የሚሰራ (የሚዘምት) ገለልተኛ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው።

441 Caledonian Road, London, N7 9BG | www.jcwi.org.uk

Registered Charity No.1117513